# የየሱስ ከሕዝቡ ጋር ተደባልቆ መኖር

## ሰንበት ከሰዓት

ለዚህ ሳምንት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት የሚከተሉትን ጥቅሶች ያንብቡ፦ ማቴ. 1:22- 23፣ ዮሐ. 1:14፣ ሉቃስ 15:3—24፣ ማቴ. 9:10—13፣ መዝ. 51:17፣

1ዮሐ. 2:16፣ፊልጵ. 2:13—15።

> **የሳምንቱ ጥናት መሪ ጥቅስ፦** "አንድ ቀን ቀረጥ ሰብሳቢዎችና 'ኃጢአተኞች' ሁሉ ሊሰሙት በዙሪያው ተሰበሰቡ። ፈሪሳውያንና ጸሐፍትም 'ይህ ሰው ኃጢአተኞችን ይቀበላል ከእነርሱም ጋር ይበላል' እያሉ አጉረመረሙ (ሉቃስ 15፡1-2)።

የአንድ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ዲያቆን የሆነ አገልጋይ በወር አንድ ጊዜ በሚደረግ የአምልኮ ሥነ ሥርዓት ላይ ለመገኘት አስራ ሁለት ሰው በሚያሳፍረው ከፍ ባለ መኪናው ወጣቶችን ይዞ ወደ አንድ ዕድሜ ጠገብ የአምልኮ ስፍራ ይወስዳቸዋል። በስፍራው ሲደርሱ ወጣቶቹ ቀደም ብለው ከመኪናው ይወርዳሉ፡፡ አብረዋቸው የነበሩ አንድ ሽምግል ያሉ በጋሪ የሚገፉ አዛውንት ግን የዲያቆኑን እጅ ጠበቅ አድርገው በመያዝ ይወርዱና አገልግሎቱ እስኪያልቅ በዚያው ሁናቴ ማለትም--የዲያቆኑን እጅ ጨብጠው እንደ ያዙ ይቆያሉ። ይህ ሁናቴ በየወሩ የተለመደ ክስተት ሆኖ ቀጠለ። አንድ ቀን ወጣቶቹ ከመኪናው ሲወርዱ በጋሪ የሚገፉት አዛውንት ግን በዚያ አልነበሩም። አዛውንቱ የትናንትን ምሽት በህይወት አልፈው በዚህ ስፍራ መገኘታቸው አጠራጣሪ ሊሆን እንደሚችል የቤተ ክርስቲያን ሠራተኞች ሲያወሩ ተሰማ። ዲያቆኑ ወደ መኖሪያ ቤታቸው አመራ። በመኝታቸው ላይ ጋደም ብለው የነበሩት አዛውንት በእርግጥም ራሳቸውን አያውቁም ነበር፡፡

ከዚያም የአዛውንቱን እጅ ያዝ አድርጎ ጌታ የዘላለም ሕይወት ባለቤት እንዲያደርጋቸው እየጸለየላቸው እያለ እኛ ሙሉ ለሙሉ ራሳቸውን የሳቱ የሚመስሉ አዛውንት እጁን ጭብጥ አድርገው ሲይዙት በእርግጥም ጸሎቱ እንደ ተሰማ አወቀ። የዲያቆኑ ዐይኖች በእንባ ተሞልተውና ሰውነቱ እየራደ ከመኝታ

ክፍላቸው ሲወጣ አንዲት ሴት ጠጋ ብላ እንዲህ አለችው "እኔ ልጁ ነኝ። የአንተን መምጣት ሲጠባበቅ ነበር። አባቴ ሲናገር 'የሱስ በወር አንድ ጊዜ እየመጣ እጄን ይይዘኛል። ስለዚህ የሱስ መጥቶ እጄን የሚይዝበትን ሌላ ዕድል እስካገኝ መሞት አልፈልግም' ብሎ ነግሮኝ ነበር" አለችኝ። –Adapted from The Least of These, a video produced by Old Fashioned Pictures (2004). Used by permission.

ክርስትና ለሆነ ሰው እንደ "የሱስ" ሆኖ እርሱን ገልጦ ማሳየት ነው። ቀጣዮቹ ትምህርቶች የሱስ አገልግሎት የሰጠባቸው ዘዴዎች ስለነበራቸው ገጽታና ቤተ ክርስቲያን የእርሱን አገልግሎት በተግባር መግለጥ በምትችልበት አካሄድ ዙሪያ ትኩረት ያደርጋል።

*እሁድ ሐምሌ 24* *Jul 31*

## ክርስቶስ የተጠቀመበት ዘዴ ብቻ

"ወደ ሕዝቦች ለመድረስ በምናደርገው ግስጋሴ የእውነተኛ ስኬት ባለቤት ሊያደርገን የሚችለው ክርስቶስ የተጠቀመበት ዘዴ ብቻ ነው። የሰዎችን በጎ አጥብቆ ይሹት የነበረው አዳኝ እነርሱን መስሎ ተቀላቀላቸው። ርኅራኄውን በማሳየትና በችግራቸው በመድረስ የልባቸው ጓዳ ቤተኛ፣ የምስጢራቸው ተጋሪ ጓደኛ--ከሆነ በኋላ 'ተከተሉኝ' አላቸው"–Ellen G. White, The Ministry of Healing, p. 143. (ማቴ. 9፡35-36)። ከላይ የቀረበውን አባባል በመጠኑ ለመተንተን እንሞክር ሁሌም ለሰብዓዊው ፍጡር በጎ የሚመኘው የሱስ ከሕዝቡ ጋር ተቀላቅሎ ኖሮ (የመገናኛ ዘዴን ቀየሰ) የሕዝቡን ችግር እንደ ራሱ በማየት ስሜታቸውን ተካፈለ (የቅርብ ትስስር ፈጠረ) በችግሮቻቸው መፍትሔ በመሆን አገለገላቸው (የቅርብ ትስስር ፈጠረ) ከላይ የተጠቀሱት ሶስት መሰረታዊ ባህሪያት አንድ ላይ ተጣምረው--የሕዝቡን ልብ ማሸነፍ አስቻሉት፡
፡

ከዚህ በኋላ "ተከተሉኝ" አላቸው (ደቀ መዛሙርቱ ይሆኑ ዘንድ) ከላይ በቀረበው የምንመለከተው ሁሉን በአንድ ያቀፈውን የወንጌል ቅርጽ ነው። ይህ የአገልግሎት አሰጣጥ ዘዴ ወንጌልን ይበልጥ በሙላት እንድናውጅ ይመራናል። የሱስ ራሱን ከማኅበራዊ ሁናቴዎች (ከቁ. 1-4) ሳይነጥል እንዲከተሉት ግብዣ (ቁ. 5) ያቀርብ እንደ ነበረ ሁሉ በተመሳሳይ የእርሱን ፈለግ መከተል ይጠበቅብናል። አንዱ ከሌላው ጋር ትስስር የነበረው እያንዳንዱ ቅደም ተከተል "የእውነተኛ ስኬት" ባለቤት ያደርጋል። የዚህ ሳምንት ትምህርት የሱስ በተጠቀመው የመጀመሪያ ዘዴ ላይ ትኩረት የሚያደርግ ሲሆን ከ7-11 ያሉት ደግሞ በቀሪዎቹ ላይ ፍተሻ ያደርጋሉ።

በመቀጠል የቀረቡት ጥቅሶች ተቀላቅሎን ስለ ኖረው እግዚአብሔር ወልድ ምን ይነግሩናል? ማቴ. 1:22-23፣ ዮሐ. 1:14።

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------
---

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------
---

እኛ ሁላችን በኃጢአት ክፉኛ የተጎዳንና ብርቱ እክል የገጠመን ቢሆንም-- እግዚአብሔር ግን ሰብዓዊውን ሥጋ ለብሶ ሁሉን በአንድ ያካተተ አገልግሎት በሰጠው

በየሱስ አማካይነት በኃጢአት ቀውስ ከወደቀው ዓለም ጋር እርቅ ፈጠረ። የሱስ አገልግሎት የሰጣቸው እነዚያ ማኅበረሰቦች እጅግ የከፉ የሚባሉ እንደነበሩ ቢታመንም--እርሱ ግን አብሮአቸው ኖረ፣ ከግለሰብ የተሟላ መልካም ስብዕና እስከ መላው ሰብዓዊ ዘር በጎነት ያለውን ጥልቅ ምኞት ገለጸ።

ፍጥረት ሁሉ በእርሱ መፈጠሩን (ዮሐ. 1:3) የሚነግረንን ይህን አስደናቂ የመጽሐፍ ቅዱስ እውነት ጊዜ ወስደው ለማሰላሰል ይሞክሩ። የሱስ ሰብዓዊውን ሥጋ ወሰደ። ይህን ሥጋ ለብሶ ከሰብዓዊው ፍጡር ጋር ተቀላቀለ፤ በተጨባጭ እንዳሳየው-- በኃጢአት የወደቀውን ዘር አገለገለ። ይህ በተስፋ የተሞላ አስደናቂ እውነት ከሌሎች ጋር ተቀላቅለን አገልግሎት እንድንሰጥ ኃይል ሊሆነን የሚገባው እንዴት ነው?

*ሰኞ ሐምሌ 25* *Aug 1*

## ጠፍቶ የተገኘው

የሱስ "ኃጢአተኞችን ይቀበላል ከእነርሱም ጋር ይበላል" (ሉቃ. 15:2) በሚል ለቀረበበት ክስ ሶስት ምሳሌያዊ ታሪኮችን በሉቃ. 15 በመንገር ቀጥተኛ ምላሽ ይሰጣል።

የሚከተሉትን ጥቅሶች በማንበብ የሱስ ለቀረቡበት ክሶች የሰጠውን ፍሬ ሃሳብ ልብ ይበሉ።

ሉቃስ15:3—7 ____________________________________________________________

ሉቃስ 15:8—10____________________________________________________________

ሉቃስ 15:11—24____________________________________________________________

እያንዳንዱ አንቀጽ የሚጀምረው ስለ ጠፋ ነገር በመናገር ሲሆን የሚያበቃው ደግሞ እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን ፍቅር በሚገልጽና ስለ መዳናችን ያለውን ጥልቅ ስሜት በሚያሳይ--መጨረሻው ደስታና ሐሴት በሆነ ውብ ትዕይንት ነው።

አንድ ቤተሰብ የትንቢት ድምፅ ተከታታይ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ማጥናት ይጀምራል። ሆኖም የቤተሰቡ አንድ አባል ትምህርቱን እየተከታተለ አለመሆኑን ሁኔታውን በቅርብ ይከታተሉ የነበሩ የቤተ ክርስቲያን መጋቢ ይደርሱበታል። ትንሽዋን ልጃቸውን ጨምሮ ወላጆች የሱስን የግል አዳኛቸው አድርገው ለመቀበል በሚያደርጉት ሂደት ፓስተሩ በመደበኛ ቤታቸው እየመጡ አብረዋቸው የሚያጠኑትን ጥናት በጉጉት መከታተል ከጀመሩ ውለው አድረዋል። ትልቁ ልጅ ግን እምብዛም ለክርስትና እምነት ፍላጎት አልነበረውም። መጋቢው በየምሽቱ ለመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ወደዚህ ቤተሰብ በመጡ ቁጥር--በጥናቱ የመካፈል ፍላጎት ያልነበረው ይህ ወጣት ክፍሉን ትቶ ይወጣል። ስድስት ሳምንታትን ካስቆጠረ አስደሳችና ውጤታማ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት በኋላ--እነዚህ ሦስት የቤተሰብ አባላት ለመጠመቅ እንዲወስኑ ፓስተሩ ጥሪ ያቀርቡላቸዋል። ሆኖም ሁሉም የየራሳቸውን ምክንያቶች በማቅረብ ለጥምቀት ከመወሰናቸው አስቀድሞ ጥቂት ወራት መቆየት እንደሚፈልጉ ይገልጻሉ።

በዚህ መሃል አንድ አስደናቂ ክስተት ይፈጠራል። ለመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ፍላጎት ያልነበረው ልጅ ጥናቱ ወደ ሚካሄድበት ሳሎን ዘው ብሎ በመግባት፤ ለጥምቀት ዝግጁ መሆኑንና ለመጠመቅ እንደሚፈልግ ለፓስተሩ ያሳውቃቸዋል። ለካስ ልጁ ከአሮጌ ተራ የገዛውን መጽሐፍ ቅዱስ ተጠቅሞ ከአንደኛ ትምህርት ጀምሮ የነበሩትን ትምህርቶች ክፍሉ ቁጭ ብሎ ሲያጠና በመክረሙ፤ ከቀን ወደ ቀን በውስጡ እያደገ የመጣውን ብርቱ እምነትና በክርስቶስ መካካት በሰዎች ፊት ቆሞ ለመግለጽ ውሳኔ ላይ ደርሶአል፡፡ ይህ በሆነ በሁለተኛው ሳምንት ተጠመቀ። ከእርሱ ጥምቀት አንድ ወር በኋላ የተቀሩትም የቤተሰብ አባላት ተመሳሳይ የጥምቀት ሥነ ሥርዓት በመፈጸም ክርስቶስን የግል አዳኛቸው አድርገው ተቀበሉ። የሱስ የተናገራቸውን ምሳሌያዊ ታሪኮች ጠለቅ ብለን ስናጤን በእነዚህ ውሳኔዎች ሰማይ ምን ያህል በደስታ እንደተሞላ መገመት እንችላለን።

የሱስ በውሃ ጉድጓዱ አጠገብ ያገኛትን ሳምራዊ ሴት፣ እምነት የነበረውን መቶ አለቃ፣ የአንድ ዓመት አገልግሎት ደሞዝ ያህል ዋጋ የነበረውን የአልባስጥሮስ ሽቶ በየሱስ ላይ ያፈሰሰችውን "ኃጢአተኛ" ሴት ጨምሮ--ራሳቸውን እንደ ማይገቡ አድርገው የቆጠሩ ታሪካቸው ያልተጻፈ አያሌ ወገኖችን ሆነ ብሎ ተገናኝቶአል።

ለቤተ ክርስቲያንዎ ተስማሚ ሳይመስሉ ቀርቶ--ይሄስ ቢቀር ብለው ለመመስከር ያመነቱበት ሰው ይኖር ይሆን? እነዚህን "ኃጢአተኞች" አቅፈውና ደግፈው የጸጋው ተቋዳሽ ለማድረግ--እርሶንም ሆነ ቤተ ክርስቲያንዎን የሚያስወጣው ነገር ምንድን ነው?

*ማክሰኞ ሐምሌ 26* *Aug 2*

## ከኃጢአተኞች ጋር መብላት

በማቴ. 9፡10-13 የሱስ ለተሰነዘረበት ወቀሳ ከሰጠው ምላሽ እንደ ግለሰብ የምንወስደው ቁልፍ መልእክት ምንድን ነው? ሆሴ 6፡6።

--------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

---

--------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

---

የሱስ በመመገቢያ ጠረጴዛው ፊት ዘና ብሎ ተቀምጦና ዙሪያውን ከነበሩ ሰዎች ጋር ወዳጃዊ አብሮነት ፈጥሮ በአንድ ላይ ማዕድ መቁረሱ--ማንም አብሮአቸው ለመሆን ከማይመኛቸው ዓይነት ሰዎች ጋር እንደ ተገናኘ ተደርጎ ታሰበ።

በእርስዎ ባህል--አብሮ ለመሆን የማይመኙአቸው ዓይነት ሰዎች ምን ዓይነት ናቸው?

--------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

---

የሱስ ከእንደነዚህ ዓይነቶቹ የሚናቁ ሰዎች ጋር በመቀላቀሉ ትክክለኝነት ዙሪያ በፈሪሳውያን ለተነሳው ጥያቄ--ከመሥዋዕት ይልቅ ምኅረት የመውደድን መልእክት ትርጓሜ እንዲማሩ ሲሞግታቸው ይታያል። “ሄዳችሁ‘ከመሥዋዕት ይልቅ ምሕረትን እወዳለሁ’ የሚለውን ቃል አጢኑ፤ ኃጢአተኞችን እንጂ ጻድቃንን ልጠራ አልመጣሁምና” (ማቴ. 9:13)። የኃይማኖት መሪዎች የገዛ እምነታቸው ክፍል የሆነውን እጅግ አስፈላጊ እውነት እንዲማሩ ከየሱስ መስማታቸው ምን ያህል አሳዛኝ ነው!

ሰዎችን አብልጦ የሚያሳስበው ችግረኞችን መጎብኘት፣ መንከባከብና ተደራሽነትን በተግባር ማሳየት ሳይሆን የኃይማኖትን መልክ ብቻ ይዞ ሥርዓቱን እየፈጸሙ መኮፈስ እንደ ሆነ በብሉይ ኪዳን ዘመን ተከስቶ ከነበረው ተመሳሳይ ችግር በድጋሚ መመልከት እንችላለን። የሱስ ይህን የብሉይ ኪዳን ጥቅስ (ሆሴ. 6፡6) ተጠቅሞ ለመልእክቱ ክብደት መስጠቱ አስደናቂም አስደሳችም ነው።

“ክርስቶስ በማቴዎስ ግብዣ እንደ ገሰጻቸው ፈሪሳውያን ዓይነት ስህተት በሺ የሚቆጠሩ ሰዎች ዛሬም ይሠራሉ። ብዙዎች የሚወዱትን አስተሳሰብ ወይም ጣኦት የሆነባቸውን ግላዊ አመለካከት ትተው ከብርሃን አባት የሚመጣውን እውነት ለመቀበል ፈቃደኞች አይደሉም። በራሳቸው ስለሚታመኑና በገዛ ዕውቀታቸው ስለሚመኩ የሚገኙበትን መንፈሳዊ ጉስቁልና አይገነዘቡም...“ስለ ሌሎች በጎ ግድ በማይለው--ከእኔ በላይ ላሳር ዓይነት ጭፍን መንፈስ የሚደረግ ጾም ወይም ጸሎት በእግዚአብሔር ዐይን አጸያፊ ነው።”–Ellen G. White, The Desire of Ages, p. 280.

የግል ምርጫዎቻችንንና መለኪያዎቻችንን እየተጠቀምን ሌሎችን በድርጊቶቻቸው መዳኘት ቀላል ነው። መንፈስ ቅዱስ ምኅረትን ወደ ጽኑ እምነት እንዲለውጥ እየፈቀድን--እኔነትን በተሰበረ መንፈስ ማስወገድ መማር ይኖርብናል።

መዝ. 51፡17 ምን እያለን ነው? የገዛ በደለኝነታችንን ማወቃችን የዚህን ጥቅስ ትርጉም በተሻለ ማስተዋል እንድንችል እንዴት ሊረዳን ይችላል?

*ረቡዕ ሐምሌ 27* *Aug 3*

## በማስተዋል መደባለቅ

በመድረኩ የቆሙት ተናጋሪ “አድቬንቲስት ያልሆኑ” ስንት ጓደኞች እንዳሏቸው ምዕመኑን ጠየቁ። በኂለኞቹ ወንበሮች ከተቀመጡት አንዱ ቀብረር ብሎ ብድግ አለና “አንድም ጓደኛ እንደሌለኝ በኩራት መናገር እወዳለሁ!” ሲል ምላሹን ሰጠ። ግለሰቡ መልካም ቢልም ነገር ግን ለዓለም ምን ዓይነት ብርሃን እንደ ነበር አስመልክቶ እነዚያ ከአንደበቱ የወጡ ቃላት ብዙ ብለዋል።

የምድር ጨው መሆናችንንና--ጨው ደግሞ ጣዕሙን ሊያጣ እንደሚችል ቀደም ብለን በማቴ. 5፡13 ተመልክተናል። አንድ የሲዶን ነጋዴ የነበረውን ከፍ ያለ የጨው ክምችት በአንድ ጥላ ስር--ሌጣ መሬት ላይ አከማችቶ ነበር። ሆኖም ጨዉ ከመሬት አፈር ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት እንዲኖረው ሆኖ በመቀመጡ የነበረውን ጣዕም ሊያጣ ችሎአል። በዚህም ተከማችቶ ከተቀመጠበት እየተጋዘ ለመንገድ ንጣፍ እንዲውል ተደርጎ ነበር። በተመሳሳይ እኛም ከዓለም ጋር ስንቀላቀል ብርቱ ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርብናል። ዓለም በዓይነቱ ልዩ የሆነውን ጣዕማችንን እንዲዘርፍ እየፈቀድንለት ይሆን? እሴቶቻችንስ ከዓለም ጋር ተመሳሳይ ናቸውን?

ከዓለም ጋር መደባለቅ እንደሌለብን አስመልክቶ ከእነዚህ ታሪኮች ምን መማር እንችላለን? ዘፍ. 13:5—13፣ 19:12—26፣ ዘኍ. 25:1—3--በተጨማሪ 1ዮሐ. 2:16 ይመልከቱ።

----------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------
---

----------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------
---

እነዚህ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምሳሌዎች በ 1ዮሐ. 2:16 በተጠቀሱት ዓይነት ዓለማዊ እሴትን መሰረት አድርገው ከሚኖሩ ሕዝቦች ጋር ተደባልቀን ስንኖር ጥንቃቄ ማድረግ እንደሚኖርብን ይነግሩናል። በወደቀው ዓለም መርኅዎች ተጠልፈን እንድንወድቅ ሊያደርግ የሚችል አደጋ የለም--ወይም የተለየ ጥንቃቄ ማድረግ አይጠበቅብንም ብለን የምናስብ ከሆነ ራሳችንን እናታልላለን። በተመሳሳይ አንዳንዶች በአሉታዊ አካሄዳቸው እንዳይበርዙን ባለን ሥጋት ራሳችንን እየሸሸግን ለሌሎች መልካም መሆን የምንችለው እንዴት ነው?

"የጽድቅ በእምነት አስተምህሮን የተቀበሉ ክርስቲያኖች ካልተለወጡት ጋር ግንኙነት ለመፍጠር አሻፈረኝ ሊሉና አንዳችም የትስስር መስመር እንዳይኖራቸው ጥረት ሊያደርጉ ይገባልን? በጭራሽ አይገባም! ከእነርሱ ተነጥለው ሳይሆን--አብረዋቸው በዚህ ዓለም ሊሆኑ የተገባ ቢሆንም፤ ነገር ግን አካሄዳቸውን ሊከተሉ፣ በነገሮቻቸው ሊመሰጡም ሆነ ልባቸውን ለአንጉል ልማዶቻቸው ሊከፍቱ አይገባም። የግንኙነታቸው ዓላማ ሌሎችን ወደ ክርስቶስ ማምጣት መሆን ይኖርበታል።"– Ellen G. White, Selected Messages, book 3, p. 231.

አድቬንቲስት ያልሆኑ ጓደኞችዎ ቁጥር ምን ያህል ይሆናል? የግንኙነታችሁ ተፈጥሮ ምን ይመስላል? የማንኛችሁ ተጽእኖ ያይላል--የእርስዎ ወይስ የእነርሱ?

*ሐሙስ ሐምሌ 28* *Aug 4*

## በጠማማ ትውልድ መሃል

በክርስቶስ የተሰጡንን ነገሮች ዓለም የመፈለጉ እውነታ ጥያቄ ውስጥ የሚገባ አይደለም። እኛን በእጅጉ ተፈላጊ ያደረገን በራሳችን የኖረን ነገር ሳይሆን በክርስቶስ ያገኘነው ማንነት ነው። ወደ ሌሎች ለመድረስ አስፈላጊ የሚያደርገን ከክርስቶስ የተቀበልነው ጸጋና መልካም ምግባር ነው። እጅግ የተትረፈረፈ ነገር ተሰጥቶን ምንም ወደ ሌላቸው አያሌ ወገኖች እንድንደርስ መጠራታችን ትክክል ነው። " 'በነጻ የተቀበላችሁትንም በነጻ ስጡ' " (ማቴ. 10:8)።

በ ፊልጵ. 2:13-15 የተነገረን ነገር ምንድን ነው? ወደ ሌሎች እንድንደርስ ለቀረበልን ጥሪ ወደ ኋላ ሳንንሸራተት በብርታታችን እንደ ቀጠልን መገኘት የምንችለው እንዴት ነው?

ራስን ከዓለም ተጽእኖ ለመጠበቅ በሚል እሳቤ በዓለም ካሉ ነፍሳት ጋር አንዳችም ንክኪ እንዳይኖር በመሻት ዙሪያ ብርቱ ጥንቃቄ ሊደረግ ይገባል። በቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊና መለኮታዊ አስተምህሮ ምቹ ቀጠና ውስጥ እየተመላለሱ ከሌሎች ጋር አለመደባለቅ በጣም ቀላል ነው። ሆኖም ይህ ከሌሎች ጋር የማይደባለቅ መንፈሳዊነት ውሎ አድሮ ራስን ብቻ ማዕከል ወዳደረገ ኃይማኖትነት ሊቀየር ይችላል። ለምሳሌ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያኖች እየሞተ ላለው ዓለም ወጥተው ከመመስከር ይልቅ አብዛኛውን ጉልበታቸውን የሚያውሉት በአምልኮ ዘይቤዎችና ኃይማኖታዊ አስተምህሮዎች ዙሪያ ፍልሚያ በማድረግ አይደለምን?

ሮበርት ሊንቲከም በመባል የሚታወቁት ጸሐፊ Empowering the Poor በተሰኘው መጽሐፋቸው ከገጽ 21-30 ባሰፈሩት ሀሳብ ስለ ሶስት ዓይነት ቤተ ክርስቲያኖች ገለጻ ያደርጋሉ። **ከማኅበረሰቡ ገለል ብላ የተቀመጠች ቤተ ክርስቲያን፦--** ይህች ቤተ ክርስቲያን ብርቱ አጽንኦት የምትሰጠው የአባላቶቿን ፍላጎት በማሟላት ዙሪያ እንደ መሆኑ ከማኅበረሰቡ ጋር ቀረቤታ አላት ለማለት አያስደፍርም።

**በአንድ ወገን ወደ ማኅበረሰቡ ያዘነበለች ቤተ ክርስቲያን፦--** ይህች ቤተ ክርስቲያን ለማኅበረሰቡ አገልግሎት መስጠት እንዳለባት ስለምታስተውል ብቻ አገልግሎት ከምትሰጠው የሕብረተሰብ ክፍል ጋር ሳትመካከርና ተገቢውን ፍተሻ ሳታደርግ ማኅበረሰቡ የሚፈልገው ይህን ነው ብላ የራሷን ግምት በማስቀመጥ-- ለማኅበረሰቡ ይበጃሉ ያለቻቸውን መርኀ ግብሮች ነድፋ ለማቅረብ ትሞክራለች። ይህ ዓይነቱ አገልግሎት ከማኅበረሰቡ ፍላጎት ጋር ስለማይጣጣም--ማኅበረሰቡ የራሴ ብሎ እንዳያቅፈው አደጋ ሊገጥመው ይችላል።

**ከማኅበረሰቡ ጋር አብሮነት ያላት ቤተ ክርስቲያን፦--** ይህች ቤተ ክርስቲያን የምትገኝበትን ማኅበረሰብ በጥልቅ ለማወቅ የሚያስችሏትን እንደ ነዋሪዎች ብዛት፣ ዕድሜ፣ ጾታ፣ የብሔር አቀያየጥ--በመሳሰሉት ዙሪያ መረጃዎችን ሰብስባ ትተነትናለች። የቤተ ክርስቲያን አባላት ከማኅበረሰቡ አመራርና ነዋሪዎች ጋር በመቀላቀል በተጨባጭ የሚያሹዋቸውንና የተቸገሩባቸውን ነገሮች ይጠይቃሉ። ማኅበረሰቡ የራሱን ግብአቶች በመስጠቱና በሂደቱ ላይ አመኔታን በማግኘቱ አባላት ለማኅበረሰቡ የሚሰጡት አገልግሎት ከነዋሪው ፍላጎት ጋር የሚጣጣምና መልካም ተቀባይነት የሚኖረው ይሆናል። እንዲህ ዓይነቷ ቤተ ክርስቲያን ማኅበረሰቡ የሚፈልገውን ዓይነት ሕብረተሰብ ለመፍጠር የሚያደርገው ትግል አካል በመሆን ዓላማውን ለማስፈጸም የምትረዳ አጋዥ ኃይል ትሆናለች። እንደ አስፈላጊነቱ በማኅበረሰብ አቀፍ ተቋማት ውስጥ ተሳትፎ በማድረግ ሕብረተሰቡ ለተቸገረባቸው አገልግሎቶች የበኩሏን እገዛ ልታደርግ ትችላለች። የማኅበረሰቡን ተጨባጭ ችግሮች ለመጋራት--ከሕብረተሰቡ ጋር በጋራ መሥራት ግድ ይላል።

*አርብ ሐምሌ 29* *Aug 5*

## *ተጨማሪ ሀሳብ*

የሚከተሉትን ጽሑፎች ያንብቡ--Ellen G. White, “Our Example,” pp. 17—28, in The Ministry of Healing; “Levi-Matthew,” pp. 272—280, in The Desire of Ages.

ቤተ ክርስቲያን የተሰጣት ተልዕኮ ለራሷ ብቻ ሳይሆን ለዓለም ጭምር ነው። ይህች ተቋም የተደራጀችው ለሌሎች አገልግሎት እንደትሰጥ ሆና ነበር። አንድ የሌላ ክርስትና

እምነት ተቋም--ቤተ ክርስቲያኒቱ የምትገኝበትን አቅጣጫ የሚያመለክት የማስታወቂያ ሠሌዳ በዋናው መንገድ መጨረሻ ላይ ለጥፎአል። ታዲያ በተባለው አቅጣጫ ተሄዶ ቤተ ክርስቲያኑ በራፍ ላይ ሲደረስ የሚገኘው ሌላው ማስታወቂያ-- "የአገልጋዩ መግቢያ" ይላል። አባባሉ ትክክለኛውን የቤተ ክርስቲያን አደረጃጀት በአንድ አጠቃሎ አልያዘም?

"አንድ ሰው በቂ ጊዜ ወስዶ የጠፉትን ሳያገለግል ወደ ጌታ የቀረበ ማንነት ሊኖረው አይችልም።" የሱስ ከሕዝቦች ጋር በመቀላቀል ረገድ ፋና ወጊ እንደ ነበር የምትናገረው ኤለን ኋይት--ቤተ ክርስቲያንም አርአያነቱን ልትከተል እንደሚገባ ትጠቁማለች። አባላት ለዚህ ምድር ጨው እንደመሆናቸው በማኅበረሰቡ ውስጥ ሊስፋፉና ሊሰራጩ ይገባል።

"አስቸጋሪውን የክረምት ወቅት በረጅም እንቅልፍ እንደሚያሳልፉ አንዳንድ የዱር አራዊቶች እኛም ራሳችንን ከዓለም ሸሽገን እንድናኖር አልተጠራንም። የሱስ እንዳደረገው ሁሉ እምብዛም ከማይወደደው፣ ከተጎሳቆለውና ከጠፋው የሕብረተሰብ ክፍል ጋር እንድንደባለቅ አስደናቂ ግብዣ ቀርቦልናል። የሱስ ከኃጢአተኞች ጋር ወዳጅ ነበር። በግብዣቸው ላይ ይገኝ የነበረውና ባሉበት ስፍራ እየሄደ ያገለግላቸው የነበረው የሱስ--ከእምነቱ ጋር በተያያዘ ግን አይደራደርም ነበር። በየሱስ አጠገብ በመሆናቸው የተለየ ምቾት ይሰማቸው የነበሩ ኃጢአተኞች ሲሆኑ፣ ራሳቸውን ጻድቃን አድርገው ይቆጥሩ የነበሩ ግን ከዚህ በተቃራኒ የነበረውን ስሜት ያስተናግዱ ነበር። በእርግጥ የሱስ ቅድሚያ የሚሰጣቸው ጉዳዮች ከፊቱ ስለነበሩ ለእንደዚህ ያለው አመለካከት እምብዛም ትኩረት አልሰጠም ነበር። የሱስ የመጣው ኃጢአተኞችን ሊያድን ነው። ምንም እንኳ አንዳንዶቹን ጻድቃን ቅር ልናሰኝ ብንችልም… ነገር ግን ያ የእርሱ የነበረ ተልዕኮ የእኛም ሊሆን ይገባል።

"አድቬንቲስቶች በምድረ ገጽ ሌላ አካል የሌለ ያህል ራሳቸውን ለረጅም ዘመን ምቾት ሊሰጣቸው በሚችል ሁናቴ ውስጥ ሸሽገው አኑረዋል። ያ ጊዜ አክትሞአል። ከዚህ በኋላ ራሳችንን ከአገልግሎት በማግለል ክህደት እየፈጸምን መኖር አንችልም። እንደ ቤተ ክርስቲያንም ሆነ እንደ ግለሰብ ወደ ማኅበረሰቡ የምንገባበት ጊዜ አሁን ነው። "–Russell Burrill, How to Grow an Adventist Church (Fallbrook, Calif.: Hart Books, 2009), p. 50.

## የመወያያ ጥያቄዎች:

1. ራሳችንን ከአገልግሎት ስናገል "ክህደት" እንፈጽማለን በሚለው ጽንሰ ሀሳብ ላይ ተወያዩ። ሃሳቡ ትንሽ ጠጠር አለ ወይስ የተነሳው ነጥብ አሳማኝነት አለው? መልስዎን በመጽሐፍ ቅዱስ መልእክት የሚደግፉት እንዴት ነው?

2. በዓለም ያሉትን ለማገልገል ከዓለም ጋር መደባለቅ አስፈላጊ ቢሆንም ድጋፍ የምናገኘውና ተጠያቂነት የሚኖረን ፈጽሞ ችላ ልንለው ከማይገባ የቤተ ክርስቲያን ቤተሰብ የሆነው ለምንድን ነው? በዓለም ተስበን ለመወሰድ ሳይሆን ዓለምን ለማገልገል በምናደርገው ጥረት እንደ ቤተ ክርስቲያን አካልነታችን አንዳችን ከሌላው ጋር መረዳዳት የምንችለው እንዴ ነው?

3. ቤተ ክርስቲያኖች ወደ ውጪ ወጥተው ዓለምን ከማገልገል ይልቅ በየውስጥ ሙግቶቻቸው ተጠምደው በሚፈጁት ጊዜና ጉልበት ዙሪያ ተወያዩ።

እነዚህን መርዛማ ሰበዞች መንቀል የምንችለው እንዴት ነው?